# የፖለቲካ እምባጮዎችና ነፍሰ ገዳዮች ትረካ

## (ከደርግ አፋኝ መኮንን እስከ ሆላንዱ ባተሌ)

አዕምሮ እሸቴ

ምርምርና ታሪካዊ ትረካ ሲነሳ ሁለት ድክመቶች ነገር ዓለሙን ያበላሻሉና መጠቀስ አለባቸው:: አንደኛው ጥራዝ ነጠቅነትን ይመለከታል::ሌላው ደግሞ ሀቅን የሚመለከት ነው:: ነፍሰ ገዳዮች ወይም የአረመኔ አገዛዝ መሳሪያ ሆነው ወንጀል የፈፅሙ ግለሰቦች በተገላቢጦሽ ከሳሽ ሆነው የሽፋንና የውሸት ታሪክ ሲተርኩ በዝምታ ማለፍ የሚቻል ካለመሆኑ በላይም ጥፋት ነው:: በሕዝብ ላብ የተማሩት ደግሞ ምሁር ሲሏቸው መሀይም፤አወቁ ሲሏቸው አላዋቂ እየሆኑና የሀቀኝነት ረሀብ እያጠቃቸው ማፈሪያ ሆነዋል:: በግርግሩ የሰማዕትና የሕዝብ ታሪክ እየተጠቃ ነውና ሁሉም ሀገር ወዳድ ዜጋ በቃችሁ ሊላቸውና ለሀቅ ለሀገር ታሪክ ሊሟገት ይገባዋል::

በአሁኑ ጊዜ ታሪክን በሀሰት የሚተርኩ ሶስት ክፍሎች አሉ፤

1ኛ/ ከደርግ ጋር አብረው የሰሩና በወንጀልም ሊጠየቁ የሚችሉት ግለሰቦችና ምሁሮች፤
2ኛ/ ከደርግ ጋር አልሰራንም ቢሉም በትግሉ ሂደት ሚናቸው አስከፊ ሆኖ ይህንኑ ለመደበቅ የሚፍጨረጨሩ፤
3ኛ/ ተራ ነጋዴዎች:: መፅሀፍ ፃፍን ብለው ሊያተርፉ የሚጥሩ አሳፋሪዎችና የወያኔ የብዕር ቅጥረኞች::

ይህ አፀያፊ የታሪክ ብረዛ ዘመቻ ያተኮረው በኢሕአፓና የየካቲትን 66 ለውጥ ባመጣውና ቀጥሎ ም አረመኔውን ደርግ በታገለው ትውልድ ላይ ነው:: ዘማቾቹ የየራሳቸው ምክንያት አላቸው:: ከብዙዎቹ ጀርባ ወያኔ ይገኛል:: ሌሎች ደግሞ በራሳቸው ታሪክ ደንግጠዋል:: በርዋንዳ፤ ቺሊና በካምቦዲያ (በውሱን ደረጃ ቢሆንም) ደም ያፈሰሱ ለፍርድ እየቀረቡ ናቸውና በሕዝብ ላይ አሰቃቂ ወንጀልን የፈፀሙ የቀልቤሳ ዕጣ ወደ ራሳቸው እንዳይመጣ በመፍራት እየተፈራገጡ ይ ገኛሉ:: በሬ ወለደ አንሶባቸው ከርግብ ዕንቁላል መርዝ አልባ እባብ ተፈለፈለ ብለው ሲሰብኩ የሚቀፋቸውና የሚያፍሩ÷ አንገታቸውንም የሚሰብሩ አልሆኑም:: ምስክርነት ሰጪ ነኝ እያለ ወደ ሚዘላብደው ወደ ደርጉ ቅጥረኛና ወደ ሆላንዱ ባተሌ ከመሄዳችን በፊት እስቲ ሌሎችን ተመሳሳይ ፍጡሮችን ጠቀስ አድርገናቸው እንለፍ::

- በተደጋጋሚ በዚያ ታጋይ ትውልድና በተማሪው አንቅስቃሴ ላይ የሚዘምቱት ፕሮፌሰር መሳይ ሰማያዊ የካድሬ ቱታ ልብስና የኢሠፓ ታጣቂ የነበሩ ናቸውና በዝምታና አርምሞ ራሳቸውን እየገመገሙ እንዴት ከፈረንሳይ ሀገር ግሬኖብል ጭፍን የማኦ ዜ ዱንግ ተከታ

ይነትና መኢሶንነት ወደ ኢሠፓ አባልና ታጣቂነት እንደገቡ በመናዘዝ ንስሐ መግባት ሲገባቸው ይባስ ብለው የበደሉትን ትወልድና ሕዝብ ባለማቋረጥ ይዘልፋሉ፡፡

- በየድረ ገፁ በታገለው ትውልድና በኢሕአፓ ላይ ነጋ ጠባ የሚዘምቱ የታሪክ ትሎችና በራዥ መዥገሮች ሌሎች የሚጠቀሱ ናቸው፡፡
- ተቀማጭነቱ በጣሊያን ሀገር የሆነ የፈጠራ ፅሁፉን በመረጃና ምርምር የተደገፈ አስመስሎ በየጊዜው የሚያቀርበው የደርግ መዝመሮችን ወደ ፈረንሳይኛ ተርጓሚ የነበረ ፤አፍራሽና ትምክህተኛ የባዕድ ቅጥረኛ ግለሰብ፤
- የወያኔ ቅጥረኞችና ለወያኔ የሚበጅ ታሪክ የሚፅፉ ሌሎች ሁሉ ፡፡ ትላንት በኢሕአፓ ላይ የአፍቅሮ ሶማሊያና አፍቅሮ ሻዕቢያ ቡትቶ ለመደረት ላይ ታች ሲሉ የነበሩ ሌሎች ደግሞ ዛሬ የሶማሊያ አክራሪዎችና የሻዕቢያ ወዳጅ ሆነዋልና ከዚሁ ከወያኔ ጎራ ለጊዜው መለየታቸው የሚጠቀስ ነው፡፡ ከመለስ ዜናዊ ተጣላን ባዮችና ጋህዲ ገለመሌን ጠራቂዎቸች በኢሕአፓና በትውልዱ ላይ የፃፉት ሀሰት ደግሞ እግዚኦ የሚያሰኝ ነው፡፡

ወያኔ ኢሕአፓንና ሌሎች ሀቀኛ ሀገር ወዳድ ድርጅቶችን በድርጅትና በግለሰብም ደረጃ ለማጥቃት ብዙ ሚሊዮን ብር መድቦ ቅጥረኞቹን ማሰማራቱ ድብቅ አይደለም፡፡ ተራራን ያንቀጠቀጠ ትወልድ ብሎ ብዙ ቅፅ መፅሀፍ ያሳተመው አስከፊ ታሪኩን በብርጭቆ ወረቀት ፍቆ አሳምሮ ለማቅረብ ነበር፡፡ ከዚህም የተነሳ በቅርቡ እነ አቶ ገብረ መድህን አርአያ ሳይቀሩ ያጋለጡትን በቀይ ሽብር ዘመን የነበረውን አፀያፊ የተባባሪ ሚና ለመሸፈንና ከተወለደ ጀምሮ ፀረ ኢትዮጵያ መሆኑን ለመደበቅ የሀሰት ታሪክ ሲያጠነጥን ኢሕአፓን መወንጀል ዋናው ተልዕኮ ሆኖ ቆይቷል፡ ለዚህም ነው ፀረ ኢሕአፓ መፅሀፍትን እያበረታታ የሚያፅፈውና በሰፊው ለማሰራጨት ከፍቶኛ ጥረት የሚያደርገው፡፡ ታሪክና መፅሐፍ ስንል ግን ጋሼ መንግስቱ ገዳሙ ገንዘብ ሲቸግረው የሚፅፋቸው ልብ ወለዶችም ቢሆኑ ጥረትን ይጠይቁ እንደነበር ማስታወስ ይኖርብናል ፡፡ አንባቢን መናቅ ሳይሆን ማክበርን የግድ ይላሉ፡፡ ታሪክ ፃፍን የሚሉ ደግሞ ታሪከን ማወቅና ከፈጠራ ወሬ መራቅ አለባቸው፡፡

አወቅን ፃፍን ባዮቹ የእኛዎቹ ግን የሚፅፉትን ጉዳይ ሀ ና ለ እንኳን የሚያውቁ አይደሉም፡፡ ሲኒማ ሰሪው አቶ ሀይሌ ገሪማ ለምሳሌ ስለ ቀይ ሽብር የማውቀው የለም እያሉ የተዛባና ሀቅ ያልሆነ አቀራረብ በጤዛ ፊልማቸው ከተዋል በሚል ተተችተዋል፡፡ ዘር ከሉጋም የሆነባቸው ዶክተር ገብሩ ታረቀኝ ደግሞ እንድ አውሮፓ አቆጣጠር በታህሳስ 1993 የወያኔን አገዛዝ የሕዝብ መንግስት ከማለታቸው ሌላ አሁን በመጨረሻ ባወጡት መፅሀፍ ውስጥ ደግሞ ኢሕአፓ ወያኔን የተጋጩት ኢሕአፓ ወያኔን ከእኔ ስር ሆነህ ትዕዛዝ እየተቀበልክ ስራ ስላለው ነው በማለት ከትግራይ ውጡልኝ ብሎ ጦርነት ለከፈተው ጠባብ ወያኔ ሽፋን ይሰጣሉ፡፡ ዶክተሩ በሚገባ የሚያውቁት ግን ሊያቀርቡት ያልፈለጉት ሀቅ ግን ግጭቱ የተነሳው ኢሕአፓ ትዕዛዜን ተቀብላችሁ በስሬ ስሩ ከሚል ምክንያት ሳይሆን ኢሕአፓ ያቀረበውን ሶስት ዓይነት የግምባርና የትብብር አማራ

ጮች ወያኔ ባለመቀበሉና የወያኔን የግንጠላ ማኒፌስቶ( መርሐ ግብር ) መሠረት ያደረገ ከትግራ ይ ውጡልኝ የሚል አቋም በማንገቡ ነበር ። በወቅቱ የወያኔ ዋና መሪ የነበረውና ጠባብነትን አክርሮ ይገፋ የነበረው አረጋዊ በርሔም በቅርቡ በፃፈው ትረካ ላይ ይህን ሀቅ ሲክድና ሲያድበሰብስ ይታያል።

ዛሬ ሊፃፍ የሚሞከረው ታሪክ የስብስቴ ጊዜ አይደለም። መረጃ አለ። ለዚህም ነው ወይዘሮ ባፌና የአቶ መለስን ልጅ አረገዙ ከማለት በፊት--ክስ ይከተላልና--ማጣራት የሚገባው። እነ እገሌ ወይም ይህ ድርጅት ይህን ይህን ስህተት ፈፀሙ ብሎ ሲፃፍ መረጃ ለሚጠይቅ መረጃው መቅረብ አለበት። አለበለዚያ ሲባል ሰማሁ ብሎ አሉባልታ አራጋቢ መሆንን በይፋ ማመን ያሻል። በመረ ጃ ያልተደገፈ ውንጀላ ( ዛሬ በየድረ ገፁ በፈሉ መህይሞች የሚለፈፈው ዓይነት) በህግ ሊያስጠይ ቅ እንደሚችል ማወቅም ያስፈልጋል። ሀቁን በዚህም በዚያም በትንሹም በትልቁም መበረዝ ወይ ም መካድ ዝቅጠት ነው። በተለይም የራስን ታሪክ ለመሸፈን ሲሆን። የደርግ አገልጋይ የነበረው ሰው ይድረስ ባለታሪኩ ብሎ የፃፈውን ልብ ወለድ በተመለከተ “ ተረት ተረት” በሚል ርዕስ በወ ቅቱ የተሰጠው የሰላ ሂስ አጋልጦትና የጽሁፉንም ኢምንትነት አረጋግጦት እያለ ይህን ሀሰት ደግ ሞ ደጋግመው ጠቅሰው ሀሰት ከሚያሰራጩት ውስጥ አንዱ ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ የተባለው የፀ ጥታ ሠራተኛ፤ የማዕከላዊ መርማሪና በአሁኑ ጊዜ በሆላንዱ ባተሌ ሆኖ ከሚኖረውና ኩባ ከተላከ ቀንደኛ ካድሬ  የሚደነቀው ነው። በዚሁ ላይ ቀጥለን የምንተች ሲሆን በቂ ምርምር ማድረግ ካልን “ ነበረ”  በሚል (2ቅፅ) የፃፈው ግለሰብ ለምሳሌ በቅፅ 1 ውስጥ በመንግስቱ ኃይለማርያም ላይ ሞት የፈረዱ የኢሕአፓ አመራር አባላት ብሎ ሲዘረዝር በዚያን ወቅት በአዲስ አበባ ያልነበ ረን የአመራር አባል ስም ከመጥቀሱ ሌላ የመኢሶን ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የነበረውንም ግለሰብ የኢሕአፓ አመራር አባል አድርጎ ያቀርባል። ይህን መሰል አሳፋሪ ጥራዝ ነጠቅነት በመሰረቱ ተራኪዎቹን ራሳቸውን የሚያስገምታቸው መሆኑ ግልፅ ነው።

ይህን ዓይነት ትዝብትን መቀበል ፈልገው በቅርቡ መፅሀፍ ካወጡት  ታሪክ ብልሹዎች አንዱ የደርግ የፀጥታ ሰራተኛ ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ የተባለው ነው። “ ምስክርነት--ከባለስልጣኑ አንደበት” በሚል በአዲስ አበባ (ግንቦት 2001) የ 348 ገፅ መፅሀፍ ያወጣው የ10ኛ የአባዲና ኮርስ ምሩቅ ነው። ይህ መፅሀፍ በአዲስ አበባ የት ማተሚያ ቤት እንደታተመ አልተገለጠም- ምናልባትም ሜጋ ከሆነና ከታወቀ  አንባቢ ይነቃብናል ተብሎ ይሆን? ሻምበል ተስፋዬ የአባዲና ፖሊስ 10ኛ ኮርስ ምሩቅ ሲሆን በዕደማርያምም ህግ ፋኩልቲም ተምሯል። የ10ኛ ኮርስ ካዴቶች ከተማሪው እንቅስቃሴ ጋር ተያይዘው ወረቀት ሲበትኑ ና ችግር ሲገጥማቸውም ካዴት ተስፋዬ ከፖለቲካ የተገለለ ቀለሜዋ ነበር። ከዚያም ዋና ስራው የሆነው በደህንነት ሚኒስቴር በጥናት ክፍል ሲሆን በማዕከላዊም በመርማሪነት ሰርቷል። የሻምበሉን መፅሀፍ የወርቅ ማዕድን ነው ብለው ያሞገሱት ሞገስ ሀብተ ማርያም የደህንነት ምክትል ሚንስቴርና አለቃውም ነበሩ።

ሻምበል ተስፋዬ መፅሀፉን ሲፅፍ ዋቢና መረጃዎቹ ምን ምን ነበሩ?

- በወያኔ እስር ቤት ሳለሁ የቀድሞ የደርግ መሪዎችና ሚኒስቴሮችን ጠየቅኩ ይላል፡፡ ለዚህ ማረጋገጫ ከሚመለከታቸው ማግኘት ባይቻልም ቢያንስ በመረጃ መልክ አቀርቧል የሚለውን መቀበል እንችላላን፡፡
- በመርማሪነቱ ካገኛቸው ሰነዶች ማለትም ቆራጥና አሰጨናቂ ከሚላቸው ገራፊዎች ጋር ሆኖ ማለት ነው፡፡ በዚህ መልክ ብርሃነ መስቀል ረዳ ሰጠ ከሚለው ቃል ይጠቅሳል፡፡(ስለ ጥቅሱ እንመለስበታለን)፤
- ከተፃፉ መፅሀፍት--ማለትም በደርጎች፤ በኢሕአፓ ነበርን ባዮች ወዘተ.... መረጃ አገኘሁ ይላል፡፡
- የራሱ የጥላቻ ቀረጢትና ተራ አሉባልታ ይዘረዝራል፡፡

ሻምበሉ ታሪክ ፀሀፊ ለመሆን ብቃቱም ችሎታውም የሌለው በመሆኑ በመሰረቱ ገና ሀ ብሎ ሲጀምር ጥላቻው ይጠልፈውና መረጃ ሳያቀርብልን ገና ኢሕአፓን ለምሳሌ ነፍሰ ገዳይ፤ ፀረ ሕዝብ ብሎ ፈርጆ ይዘልፋል፡፡ ሳያጠና የደመደመ ነውናም ብዙዎቹ ትረካዎቹ ለደረሰበት የስሜ ት ድምዳሜ ማጠየቂያ እንዲሆኑ የተለጠጡ ወይም ዘንድሮ መባል እንደተጀመረው የተፈበረኩ ናቸው፡፡ ያንን ታሪካዊ ወቅት በተመለከተ  የሻምበል ተሰፋዬ ተልዕኮ (ይህም ነው የሆላንዱን ዶክተር በሉኝ ባተሌ ያስደሰተው)

- ያ ትወልድ መዓት አመጣ
- ለቀይ ሽብር ተጠያቂ ኢሕአፓና መኢሶን ናቸው
- ኢሕአፓ የሶማሌ ወረራን ደገፈ፤ ኢትዮጵያዊ መኮንኖችን ረሸነ ፤ለደርግ በኤርትራ ሽንፈት ተጠያቂ ኢሕአፓ ነው፤
- ተራማጁ ምሁር ሀገርን አጠፋ (ለዚህም ማስረጃ ምሁር መባል የተሳነውን ሌላ የሆላንድ ምርት የደርግ የሕዝብ ድርጅት ባለስልጣንና ተረት ተራኪ ይጠቅሳል!)

በሚል መልዕክት ለማስተላላፍ ነው፡፡ የሆላንዱ ባተሌ ዶክተር ደግሞ ለዓመታት ይህንኑ ሲለፍፍ የከረመና እስካዘሬም እንዴት ለኩባ ትምህርት በደርግ እንደተመለመለ ማስረዳት የተሳነው ነውና የሻምበሉን የአማርኛ መፅሀፍ በእንግሊዝኛ በምርቃና ተችቷል፡፡

ሻምበል ተስፋዬ የደርግ የደህንነት ሚኒስቴር የጥናት ክፍል ባልደረባ ነበረና በመፅሀፉ የሰፈሩትን በሬ ወለደ የ "ጥናት" ውጤቶች ስናነብ ደርግ ይህን ዓይነት መረጃ እየተመገበ 17 ዓመት መበርከ ቱም ተዓምር ሆኖ ይገኝ እንጂ ለውድቀት የተዳረገው በእንደነዚህ ዓይነት እርባነ ቢስ ሰዎች በመታጀቡ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በመፅሀፉ በርካታ ገፆቸ ሻምበሉ ለሚያቀርባቸው አስደ ናቂ ክሶች ከራሱ ድንፋታ ባሻገር ምንም ተጨባጭ ማስረጃ አያቀርብም፡፡ ሻምበል ተስፋዬ በገፅ 97 ጀምሮ ትንሽ  ስለ ኢሕአፓ ብሎ ያተተው ሁሉ ሲነበብ ምንኛ ይህ ሰው በቅዠትና በጥላቻ

ዓለም ሲኖር መቆየቱንና አሁንም ለዘመኑ ባለስልጣኖች ማደሩን የሚያሳይ ይሆናል፡፡ ኢሕአፓን በሰፊው ለማጋለጥ ዝግጅት አለኝ የሚለው ሻምበል የሚከተለውን በመቀባጠር ይጀምራል፤

> " ኢሕአፓ ገና ከመነሻው አዲስ አበባ ጠንሳሽ መሪዎቹ በራሳቸው መንፈስ የተንቀሳቀሱ ሳይሆን በዚያን ጊዜ አዲስ አበባ ውስጥ በነበረው የአልጄሪያ አምባሰደርና በስሩ በነበረው የአልጄሪያ የውጭ መረጃ ድርጅት የተፈለፈሉ መሆኑን የዚያን ጊዜው የመረጃ ቢሮው መዛግብት ይናገራሉ፡፡"

የጉድ ጅራት ረጅም ነው፡፡ ሻምበሉ ቢያንስ ኢሕአፓን ሻዕቢያ ወለደው የሚለውን የደርጎች ክስ በ "መረጃ" ያስተባብላል ማለቱ ነው፡፡ ከስንቱ ሌላ ቀባጣሪ ሊጣላ ነው! ለመሆኑ በዚያ ጊዜ የአልጄሪያ ኤምባሲ በአዲስ አበባ ነበረ? ከነበረስ ምንኛ በኢትዮጵያ ጉዳይ ቢጨነቅ ነው (ከነግብፅና ሌሎች በላይ) ተማሪዎችን ሊያደራጅ የተነሳው? ሻምበል ተስፋዬ የአረመኔ አገዛዞች ቅጥረኛ ነበርና ለሀገር ሊታገሉ የተነሱትን መወንጀሊያ ቢያጣ በሬ ወለደ ውሸቱን መረጃ ብሎ ማስፈር ተገደደ፡፡ በደህንነት ሚኒስቴር የሰሩ ብዙዎች ግን ይህ እሱ የሚጠቅሰውን ሰነድ መቸም ያላዩ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ፡፡ ሰነዱ ቢኖርማ ኖሮ ደርግም በይፋ ከሶ በተጠቀመበት ነበር፡፡ በገፅ 98 ሻምበሉ ብርሃነ መስቀል ከሰጠው ቃል ብሎ ያቀረበውም አልጄሪያ የነበሩት ከነማን ማን (ኢትዮጵያውያን ጋር) መገናኘታቸውን ይዘረዝራል እንጂ በአልጄሪያ የስላላ ድርጅት "እየተደገፍን" የሚል ምንም ዕሁፍ የለበትም፡፡ ሻምበል ግን ለጥጦ መዋሸት የተካነበት ስራ ነው ና ይቀጥፋል፡፡ " በአልጄሪያ የፔትሮ ደላር ፍሰትና የስለላ ድርጅት እርዳታ" ኢሕአፓ መስራቾ ችም መስራች ስብሰባ ማድረጋቸውን ሻምበሉ ሀቅ ብሎ ያቀርባል፡፡ ስብሰባውም በአንድ የምዕራ ብ ጀርመን የውጭ መረጃ መኮንን መኖሪያ ቤት ነበር ሲል ሻምበል ተሰፋዬ የጥናትን ሳይሆን የቅዠትን መረጃ በዚሁ ገፅ አስፍሯል፡፡ ለመሆኑ ፀረ አምፔሪያሊስት ነኝ ይል የነበረው የወቅቱ የአልጄሪያ መንግስትና የምዕራብ ጀርመን የስለላ ድርጅት አብረው ይሰሩ ነበር? እነ ሻምበል ተስፋዬ ዓይነቶቹን ቅዠታሞች ያቀፈው ደርግ ተደናግሮ ለጠላቶቹ ሰለባ ቢሆን ከቶስ ምን ያስገርማል? በአልጄሪያ የነበሩትንም ታጋይ ወጣቶች በአልጄሪያ አንጎላቸው ታጠበ ይላል? ለመሆኑ የአልጄሪያ ስትራጂያዊ ፀረ ኢትዮጵያ ጥቅም ምን ነበር? ኢትዮጵያኖችስ ሁሌም ለራሳ ቸው ማሰብ የሚያቅታቸው ፍጡሮች ሆነው ነው አንጎላቸው በአላፊ አግዳሚ አለሳሙና የሚታጠበው?!

ሻምበሉ ኢሕአፓን ይጠላል፡፡አብዮቱ የመጣበት አድሃሪና ሆዳም ዜጋ ነውና አያስገርምም፡፡ ለለ ወጥ የታገለው ተራማጅ ምሁርም በእሱ መወገዙ የሚጠበቅ ነው፡፡ ሻምበሉ በጥላቻ የተቃኘ ነው ና ሀቅና መረጃን ያደባያል፡፡ የኢሕአፓ የሡራዊት መስራቾችን ስም ሲዘረዝር ለምሳሌ ወደ ጫካ በመጀመሪያ ያልገቡትን ስዩም ከበደና ዘርዓብሩክ አበበንም ይጨምራል፡፡ (ስዩሜ በአዲስ አበባ ከደረጉ ነፍሰገዳዮቸ ጋረ ተታኩሶ ሲሰዋ ዘርዓብሩክ ደግሞ ከነሙሉጌታ ሱልጣንና ውብሸት ረታ ጋር በደርግ ተረሽኗል)፡፡ ሻምበሉ ስለ ኢሕአፓ ያለው መረጃ አስቂኝ ነው፡፡ በገፅ 100 ሻምበሉ

ጠቀስኩ የሚለው ተራኪ ዘገባም ቢሆን ከሀቅ የራቀ መሆኑን ከዚህ በፊት ተተችቷል፡፡ ዶክተር ተስፋዬን ዘረኛ ለማለት በአባዲና ሲያስተምር ከትግሬ ካዴቶች ውጭ አያናግርም ብሎ ሻምበሉ በአሳዛኝ ደረጃ ይዋሻል (ምናልባትም ካዴት ተስፋዬ እንኳን አስተማሪ ተማሪዎችም የሚርቁት ስነ ፍጥረት ነበረ ብንልስ?) ፡፡በዚህ መልክ የዘረኝነት ሽታውም ያልደረሰውን ተስፋዬ ደበሳይን ም የተሰዋው የሻዕበያን ምስጢር ለመጠበቅ ነው ብሎ ያጥላላል፡፡ ይህ ትምክህተኛ ሻምበል ባስገ ረፋቸውና በተሰዉ ጀግኖች ላይ መቀለዱ ነው!! የሻምበሉን አያሌ ሀሰቶች መጥቀስ ይቻላል፡፡ ጉንጭ አልፋ ነው፡፡ ተጀምሮ እስኪያልቅ በኢሕአፓ ላይ ውሸት ና ቅጥፈት ነው፡፡ የወያኔን ልብ የሚያሞቅ ውሸት፡፡ ሻምበሉ ለምሳሌ የደርግን የደቀ መሀሪ ሽንፈት በደርግ አመራር ጉድለትና ስህተትና ከሕዝብ መነጠል መሆኑን ክዶ (በገፅ 101) በሻምበል ነጋሽ ዘርጋው መሪነት የደርግ ጦር ለጥቃት ተጋልጦ ተመታ ብሎ ይዘግባል፡፡ ሻምበል ነጋሽ የኢሕአፓ አባል ነው ይለናል ሻም በል ተስፋዬ--ማን ነገረው? አስጠቅቶ ተሰወረ ይላል፡፡ በአንድ ሻምበል ሻጥር ብቻ ሙሉ ከተማ በጠላት ይያዛል? መረጃ አልባ የሀሰት ውንጀላና ክስ ነው ይሄ? ሻምበል ተሰፋዬ በሶማሊያ ግንባ ር ደግሞ ሀገር ወዳዱ ጦር የዚያድ ባሬን ጦር ሲጋፈጥ የኢሕአፓ አባል መኮንኖች ከጀርባ ረሸኑ ት ይላል? መረጃ? ባዶ! ስንት ቢሆኑ ነው እነዚህ የኢሕአፓ መኮንኖች ይህን ሁሉ የፈፀሙት? ጉድ እንደገና! የደርግን የሀሰት ክስ ማሽከርከር ብቻ! ሻምበል ተስፋዬ መዋሸት እንጂ የውሸቱ መነሻ መሰረት መኖር አለመኖሩም ግድ የለውም፡፡ ወደ ሜዳ ያልገቡትን ገቡ እንዳለው፤ ለአልጄ ሪያ የስለላ ድርጅት የፈጠራ ሚና እንደሰጠው ሁሉ፤ጌታቸው ማሩ ሲገደል ተሰፋዬ ደባሳይና ክፍሉ ታደሰ ቆራርጠው ሊጥሉት ሞከሩ ይላል፡፡ በዚያን ወቅት ማለትም ጌታቸው ተገደለ በተባ ለበት ጊዜ ለመሆኑ ተስፋዬ ደበሳይ በሕይወት ነበር? ሻምበሉም በገፅ 108ና 109 ስለ ኢሕአፓ የሚያቀርበው ምንኛ ደርጉ ደካማ መረጃ እንደነበረው የሚጠቁም ነው፡፡

ሻምበሉ ብዙ አላዋቂዎች ሲሉ እንደ ከረሙት የደርጉን ሻምበል ዓለማየሁ ኃይሌን በኢሕአፓነ ት ይመድባል/ ይከሳል፡፡ ይህን ስህተቱን ፍቅረስላሴ ወግደረስም ይጋራዋል፡፡ ፀሀፊው በገፀ 91 የጠቀሰው ፍቅረ ስላሴ የሚከተለውን ተናግሯል ተብሏል፤ “ እነ አለማየሁን በኢሕአፓ ናታቸው በእጅጉ እታገላቸው ነበር፡፡..... እነ ብ/ር ጄኔራል ተፈሪ በንቲ ልዩነታችንን በጠረጴዛ ዙሪያ እንፍታ፤ ብሔራዊ ዕርቅ እናድርግ ሲሉ እነ መንግስቱ በመኢሶን ግፊት እርቅ የለም በማ ለታቸው የጥር 26 ቀን 1969 ሁኔታ ተከሰተ፡፡ የብሔራዊ እርቅ ጥሪው ትክክል ነበር፡፡ ችግሮች ን በጠረጴዛ ዙሪያ ተወያይተን እንፍታ ማለታቸው ምንም ጉዳት አልነበረውም፡፡ ቢሳካ እጅግ ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ ብቻ ጥሪውን ኢሕአፓ እንደማትቀበለው እርግጠኛ ነበርኩ፡፡ ቢሞከ ር ቢያንስ ከታሪክ ተወቃሽነት በዳንን፤ እነ ተፈሪ በንቲም ለሕልፈት ባልበቁ ነበር፡፡ አልሆነም፡፡ ጥሪው በተደረገበት ዕለት ከሰዓት በኋላ መኢሶኖች አሲረው በመንግሥቱ ኃይለማርያም መሳሪያ ነት ' ቅዱሱን ጥሪ አከሸፉት'፤ ለእነርሱም አልበጃቸው፡፡” (ስርዝ የተጨመረ )

ፍቅረስላሴ በዚህም ለሰለስ ባለ ደረጃ ፀፀት ማሰማቱና እንደ ጎንደሩ ጭራቅ መላኩ ተፈራ ያደረግነው ሁሉ ትክክል ነበር አለማለቱ ደግ ሲሆን በሌላ በኩል ግን ጥሪውን ኢሕአፓም

አትቅበለውም ነበር ማለቱ ከጥላቻው የመጣ ድምዳሜ መሆኑ ግልፅ ነው። ድርጅቱ ቀደም ሲል ለቀረበው የግንባር ጥሪም አዎንታዊ መልስ የሰጠ የነበረ ሲሆን ለዚህም ለነተፈሪ በንቲ ጥሪ መልሱ ቀና ይሆን እንደነበር መገመት ይቻላል። ቢያንስ ፍቅሬ ከሚጠቅሳቸው ከነ ሻለቃ ሞገስ (የኢሕአፓ አባል) ና መለስ ማሩና በእጅ አዙር ቢሆንም ከብጄኔራል ተፈሪ በንቲ ዓይነቶቹ ጋር ግንኙት እንደነበረው ተገልጧል። ደርግ ውድቀት አካባቢም ለተደረገ ጥሪ ኢሕአፓ በኢዴኃቅ አማካይነት የሰጠው ምላሽ የእምቢታ አልነበረም።

ሻምበል ተስፋዬ ርስቱ ዋናው ዓላማው በዚያ ትውልድ ላይ ለደረሰው ጭፍጨፋ እኩል ተጠያቂ መኢሶንና ኢሕአፓ ናቸው፥ ደርግም ተጎትቶ ገባ እንጂ ሽብሩን የጠነሰሰው ወይም የፈለገና ያካሄደም አልነበረም ብሎ ለማተት ነው። ይህ ነው የሆላንዱን ባተሌና የቀድሞ የኩባ ካድሬና ያመረቀነው። ይህ የሆላንድ ባተሌ ለዓመታት የሚያቀነቅነው ጆሮን ኮስኳሽ ዘፈን ይኸው ነው-- ኢሕአፓና ያንን ትውልድ በጭፍኑ ማውገዝና ለስርዓቱ ሽብርና ወንጀል ተጠያቂ ማድረግ። የመኢሶን አመራር አባል የነበረው ዶክተር ወርቁም በፃፈው መፅሃፍ ይህንኑ ድምዳሜ ገፍቷል " መኢሶንና ኢሕአፓ እርስ በርስ ተፋጅተው ወታደራዊ አምባገነኖችን አጠናከሩት"፡ (ያኔ እሱ የደርግ ተባባሪ መሆኑን ባያነሳም)። መኢሶንና ኢሕአፓ ፖለቲካ አቅዋማቸው አንድ ነበር ወይም መኢሶን ፣ ኢሕአፓ፣ ደርግና ወያኔም ያው ርዕዮታቸው አንድ ነበር የሚሉ ክፍሎች እውነቱን ለማወቅና ለመናገር ምርምርና ጥናት ማድረግ የከበዳቸው ሰነፎች ናቸው። ዛሬማ ይባስ ብሎ የመሬት ለአራሹን መፈክር ለማውገዝ የሚጮሁ ምሁር ነን ባዮች በርከት ብለዋል። ጉድ አይሰማ ጆሮ! ሻምበል ተስፋዬ ራሱ ባቀረበው ፅሁፍ የመንግስቱን ሀገር አጥፊነት፣ ጦሩን እንዴት እንዳዳከመውና እንደበተነው፣ ግብዝነቱንና አምባገናነዊ መሆኑን በበቂ አቅርቦታል።ግን ለዛሬዎቹ አምባገነኖች ደግሞ መታያ ና ስለት /በዕጣንና ዘቢብ ፈንታ ኢሕአፓ/ መቅረብ አለበትና ሁሉንም ጥፋት ኢሕአፓ ላይ መለጠፉን መርጧል። በመፅሀፉ የጠቀሰው ሻለቃ ካሳዬ አራጋው ግን ደርግን ሲገመግም (ገፅ 58) " <u>ኢትዮጵያዊ መንግሥት ቢኖር እኮ መታሰር ቀርቶ ተቆራርጠን መገደል ሲያንስን ነው</u>" ብሏል (ስርዝ የተጨመረ) ። አዎን እነ ተሰፋዬ ርስቱና መሰሎቹ ዛሬ ሊያሞግሱትና ጀግናም ብለው ሊሸላልሙት የተነሱት ያ አገዛዝና መሪዎቹ መታሰር ሲያንሳቸው ነው።

መኢሶንና ኢሕአፓ የተለያዩት ወይም ቀደም ሲል ተራማጅ ምሁራንና ተማሪዎች የተጋጩት በቃላት ድርድር አይደለም። የ "ቸ" ና "ሸ" ልዩነት በዕርቃኑ በጥራዝ ነጠቆች ለማሾፊያ ቢቀርብም የነበረው ልዩነት የአመለካከትና የፖለቲካ አቅዋም ልዩነት ነው። ሁለቱ ድርጅቶች ልዩነታቸውን ለማጥበብ በአዲስ አበባ ተገናኝተው (ተስፋዬ ደበሳይና ኃይሌ ፊዳ) ጥረዋል፡ግን አልተቻለም። ድርጅቶች ለስልጣን ሲዋደቁ ለደርግ ተመቸው የሚለውም የነበረውን ሂደት በሚገባ መገንዘብ ያቃተው ድምዳሜ ነው። ድርጅቶች ለስልጣን ታገሉ ብሎ በክስ መልክ ማቅረብም አላዋቂነትን ያጋልጣል-- የፖለቲካ ትግል ለፖለቲካ ስልጣን ነው እንጂ ቀደም አንድ ተቺ እንዳለው የማንንም ጎፈሬ ለማበጠር አይደለም። ቁምነገሩ ስልጣን ለማን፣

ምን ዓይነት ስርዓትን እውን ለማድረግ ወዘተ የሚለው ነው:: ዛሬ ምንም የረባ የፖለቲካ ልዩነት ሳይኖራቸው የሚፈረካከሱትን ስናይ ቢያንስ በዚያን ዘመን ልዩነቶች ራዕይና መስመርን ም መሰረት ያደረጉ መሆናቸውን ዳግም እንድንገነዘብ ይገፋፋናል:: ከርክሩና እሰጥ አገባው በፖለቲካ ጥያቄዎችና መርሆች ዙሪያ ነበር:: ከደርግ ጋር እናብርና ደርግ ይወገድ የሚሉት አቀዋሞች ሊተቃቀፉ የሚችሉ አልነበሩም:: ዛሬም ቢሆን ከወያኔ እናብርና ወያኔ ፀረ ሕዝብ ነውና በትግል እናስወግደው የሚሉት አቀዋሞች አንድ ላይ ሊሰምሩ አይችሉም:: በፖለቲካው ትግል ኢሕአፓ ሰፊ ደጋፍ ማግኘቱን ሻምበል ተስፋዬም መካድ አልቻለም--ግን ተስፋዬ ለራሱ ጥላቻ መልክ ለመስጠትና አዲሱ ጌቶቹን ለማስደሰት ሀሰቱን ሲተርት እንዲህ ይላል

" ኢሕአፓ በደርግ አባላቱ በዓለማየሁ ኃይሌና ሞገሥ ወልደ ሚካኤል ሥልጣን ሙሉ በሙሉ እየተደገፉ በፖሊስ ማርቼዲስ መኪና እየተረዱ ሌሊት የአዲስ አበባ መንገዶችን በቀይ ቀለም፣ የስልክና የኤሌክትሪክ መስመሮች የኢሕአፓን ቁራጭ ቀይ ጨርቅ ሲያንጠለጥሉ እያደሩ፣ በእነ አምሐ አበበ እየተረዱ ባንክ ዘረፋውን፣ የፖሊስ ኮሌጅ መሳሪያ ንጥቂያውንና ቀን በቀን ንፁሐን ዜጎችን መግደል መቻሉ ከሁሉ በላይ አደረገው::" (ገፅ 81)

ዛሬ ጀግናው ሻምበል አምሐ ፣የተስፋዬ ዓይነቶችን ቅጥረኞች ሲታገል የተሰዋው የኢሕአፓ ልጅ በሕይወት ባይኖርም ብዙ ሺ የኢሕአፓ አባላትና ሽብሩን የኖረው ሕዝብ ሁሉ በተስፋዬ ርስቱ ላይ " ይድፋህ አቦ! ርካሽ ዋሾ" እርግማን ቢያሰማ የሚፈረድበት አይሆንም:: ኢሕአፓ ንፁሃንን ገደለ ባይ ይህ ሀፍረተ ቢስ ሻምበል ስመ ጥር የሚላቸው፣የሚያደንቃቸው ገራፊዎችና ገዳዮች፣ ሰው በላዎች ናቸው ለእሱ ንፁሃን! ከዚህ በተያያዘ ቁልፉ ጥያቄ ለመሆኑ ያኔ አንተ የት ነበርክ የሚለው ይሆናል? ሻምበሉና መሰሎቹ ቀይ ሽብሩን አፋፋሚ፣መርማሪና አሰቃይ፣ ነፍሰ ገዳዮች ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ እንደ ሆላንዱ ባተሌ በአረመኔው አገዛዝ ወይ ኩባ ወይ ምስራቅ አውሮጳ የተላኩ አማኝ ካድሬዎች ነበሩ:: ዛሬ የነ ስዬ አብርሀ " አርበኝነት" እንደ እሬት እንደ ሚጎመዝዘን ሁሉ የትላንት አራጆች፣ የህፃን ሳይቀር ስጋ እየቦጨቁ መርማሪዎችና የአረመኔው ቡድን ጀሌዎች ዛሬ ተመልሰው የሀሰት ታሪክ ሲፅፉ፣ በሰለባቸው ዳግም ሲያጓሩና የሰማዕትና ሕዝብን ታሪክ ሲያቆሽሹ ማየቱና መስማቱ ያቆስላል::

ቀይ ሽብርና ከዚያም በፊት የነበረው (ጌታቸው ሺበሺና አሊ ሙሳ " ዙረት"--አስበ ተፈሪ፣ ጅማ) ግድያ ሁሉ የደርግ አገዛዝ ድርጊት ነው:: ለዚህ ደግሞ መረጃውና ዝርዝሩ በየጊዜው ቀርቧል:: ኢሕአፓ በአምባገነኑ ላይ የግድያ ሙከራ ያደረገውም ሆኖ የመከላከል እርምጃ የወሰደው ከዚህ ሁሉ ግድያ በኋላና አጠቃላይ የሆነ የድምሰሳ ጦርነት ሲታዋጅበት ነው:: ይህን የሚክደው ሻምበልና መሰሎቹ ኢሕአፓ ተኩስ ከፍቶ፣ ሰወ ገድሎ፣ የሽብሩን አዙሪት በነጭ ቀለም ጀመረ ይሉናል:: ነጭ ሽብር ቀይ ሽብር ከሶቭየት ኅብረት የቦልሼቪክ ተመክሮ በቀጥታ በጥራዝ ነጠቅነት የተቀዳ ነበር-- አምስተኛ ረድፍ ይሉት የነበረውም ለህገራችን ሕዝብ ባዳ--

ትርጉም አልባ ነበር፡፡ ሻምበል ተስፋዬ ሲያመቸው የይድረስ ባለታሪኩን ትረካ ሀቅ ብሎ ሲቀበል ( በፈረደበትና ባልገባበት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ላይም ያ ፀሀፊ የሚያጮኸውን የጭቃ ጅራፉን ጭምር) በሌላ በኩል ደግሞ ሻዕቢያ ኢሕአፓን በማደናቀፍ ይኸው ፀሀፊ የፃፈውን ከቶም አያነሳም፡፡ ወያኔና ደርጎች አለምክንያት ይህን የተስፋዬን መፅሀፍ ለያደንቁ አልተነሱም--ውሸታቸውን ሁሉ አቀናጅቶ፤ ወንጀላቸውን ደብቆ፤ ጠላታቸውን ኢሕአፓን አውግዞና ያው በደርግ ቋንቋ በቅጥረኛ ነፍሰ ገዳይነት ሰይሞ በሬ ወለደ እናንት ግን ነፃ ናችሁ ከሂደቱ ስለሚላቸው ነው፡፡ እስቲ ወደ ክሶቹ እሥንግባ፤

1/ የሶማሌ ወረራ/የኦጋዴን ጦርነት

ሻምበል ተስፋዬ የደርጉ መርማሪ የአለቆቹን የሀሰት ጫጫታ በማስተጋባት ኢሕአፓ የሶማሊያን ወረራ ደግፎ ጉዳት በሀገር ላይ አድርሷል ይላል፡፡ ደርግም ሻምበሉም ለዚህ መረጃ አቅርቡ ሲባሉ የሚያቀርቡት የለም--ግን የሀሰት ክሱን ከማነብነብ ተቆጥበው አያውቁም፡፡ ሻምበሉ በዚህ የቀይ ሽብር ወንጀለኞችን ባስደሰተ መፅሀፉ በዚህም በዚያም ኢሕአፓ ዚያድ ባሬን ረድቶ ለሀገር በሚታገሉ መኮንኖች ላይ ከጀርባ እየተኮሰ ጉዳት አደረሰ ይላል፡፡ በባዶ! ኢሕአፓ የዚያድ ባሬን ወረራ ገና ሲጀምር ጀምሮ ተቃወመ እንጂ አልደገፈም፡፡ ኢሕአፓ ያኔ ዚያድ ባሬን ደግፎ ከሶማሌ ወራሪ ጦር ጋር ቢሰለፍ ኖሮ ድርግ ተብዬው ይጠፋ አንደነበር የዚያን ጊዜ ተጨባጭ ሁኔታ የሚያውቁት ሁሉ የሚረዳው ነው፡፡ኢሕአፓ ግን ያን አላደረገም፡፡ ጦርነቱን በማውገዙ ዚያድ ባሬ ኢሕአፓን በጠላትነት ፈርጆ ብዙ የኢሕአፓ አባላትን ፈጀ ፡፡ የተሰደዱትንም አማራ እያለ አሰቃየ፤ ገደለ እንጂ ተንከባክቦ አልያዛቸውም፡፡ የሸለምቦጥና ሌሎች ማጎሪያ ሰለባዎች የሆኑ ሁሉ የሚያውቁት ሀቅ ነው ፡፡ (የአሊ ሰዒድንም አስደናቂ ፊልም--የትውልድ ትውስታዎች-- ይመለከቷል)፡፡ የኢሕአፓ አባል መኮንኖች ለሀገራቸው በየግንባሩ ወድቀዋል፡፡ በደርግ በራሱ ተጨፍጭፈዋል፡፡ በውሱን ደረጃ ዝርዝሩን እንጥቀስ--

በነገሌ ግንባር--መቶ አለቃ ጌታቸው ገብረ መድህን፤ አስር አለቃ ቦጋለ መኮንን፤ ወታደር አብዲ ሰንደሎ፤ ወታደር ተስፋዬ ደመሳ፤ ወታደር ተካ መኮንን፤ ወታደረ ገብረ የሱስ ጎሳ፤ ወታደረ ደምሴ ገብረ ስላሴ፤ ወታደር ጎሳዬ ሽብሩ፤ ወታደር ምንተስኖት ዛፉ ወዘተ

በጂጂጋ ግንባር-- በቀለ ንጋቱ የሐረር አካዳሚ ምሩቅ ከ 20 ሌሎች ጀግኖች ጋር በደርግ መኮንን በሻለቃ መኮንን ወልደ ማርያም ሀይሌ በቆሬ የተረሸነ ፤ ሀምሳ አለቃ አሸናፊ የመሳሪያዎች አዋቂ፤ ምክትል መቶ አለቃዎች እንዳለ ወልዴና ባሳዝነው መካሻ፤ በኦጋዴን በውጊያ የተገደሉት ምክትል መቶ አለቃ ደጀኔ ድል ነሳው፤ ዳባ ታፈሰ ፤ዳታቸው ይሁኔ፤ በሀረር የተረሸኑት ምክትል መቶ አለቃ ነገደ አምሐ ፤ፀጋዬ አበራ፤ ወዘተ፡፡ ምክትል መቶ አለቃ ሙሉነህ አዳል

በጎዴ በዚያድ ባሬ ወታደሮች ተከቦ በጀግንነት ተዋግቶ በደናን አደርጎጥሶ ከነወታደሮቹ ወደ

ባቢሌ ካመለጠ በኋላ በሐረር ኢሕአፓ አባል ነህ ተብሎ በደርግ ተረሽኗል። ዛሬ በሕይወት ያሉ የሐረር አካዳሚ፣ የአባዲና፣ የሆለታ ምሩቅ መኮንኖች ስንቱ ጀግና መኮንን ኢሕአፓ ተብሎ ለመረሸኑና ስንቱ የኢሕአፓ አባል መኮንን ለሀገሩ ብሎ በየግንባሩ ለመሰዋቱ ምስክርነት ይሰጣሉና ለታሪክ አጥፊው ሻምበል የሕዝብ ምላሽ አፈር ያብላህ የሚል መሆኑ ግልፅ ነው። ኢሕአፓ ለኤርትራ ግንባሮች ትላንትም ሆነ ከዚያ በኋላ መሳሪያ አለመሆኑ በተለይ ቡችላቸው ለነበረው ወያኔ ግልፅ ሆኖ ሳለ የሻምበል ተስፋዬ ኢሕአፓና ሻዕቢያ አንድ ነበሩ ጫጫታ ማንን ም አያሳምንም። ይህን በተመለከተ ሀቁ ብዙ ጊዜ የተነገረ ስለሆነ ለገማ ለገለማ ቅጥፈት ቦታ መስጠቱ ጊዜን ማጥፋት ነው። ለኤርትራ ሽንፈት ተጠያቂ መንግስቱ ኃይለ ማርያም ነው። ጦሩን የፈታው፣ ጄኔራሎቹን የረሸነው ኢሕአፓ ሳይሆን መንግስቱ ነው። ራሱ ተስፋዬ ርስቱ በመፅሀፉ ይህንኑ በሚገባ ያስቀምጠዋል--ግን የራሱን መፅሀፍ ገና አላነበበውምና ኢሕአፓ ኤርትራን አስበላ ብሎ ሊከስ ይዳዳል። ኢሕአፓ ሳይፈጠር ለተከሰተ ችግር ሊጠየቅ አይገባው ም። ኢሕአፓ መንግስት አልነበረም-- ጦሩን ሊፈታ ሆነ ለሽንፈት ሊያደርሰው አይችልም። ጥፋቱ የደርግ ነው--የሻምበል ተሰፋዬና የሆላንዱ ባተሌ መንግስት። አባ በበሉ እማሆይ አገሱ ተብለው መከሰስ የለባቸውም።

ሻምበል ተስፋዬ ርስቱ የማዕከላዊ መርማሪ ነበር። መርማሪ ምን ማለት እንደሆነ ስየሉን የተቀበ ሉት ያውቁታል። የሻምበሉ የኮርስ አባላት ከሕዝብ ጎን ሲቆሙ ሻምበሉ ከአረመኔው አገዛዝ ጎ ን ተሰልፎ ስንቱን ሲያሰቃይና የሕዝብን ትግል ሲበድል ሲያፍን ቆይቷል። ዛሬ ደግሞ ወንጀለኛ ን አቃፊ የሆነ አገዛዝን አገኘና በወያኔ ዋና ጠላት በኢሕአፓ ላይ ይረባረባል። በንስሐ ፈንታ ውንጀላ! ካሳዬአራጋው እንዳለው ሻምበሉ እስር ሲያንሰው ነው። በደህንነት ሚኒስቴር ውስጥ ሕዝባዊ አቅዋም ይዘው የነበሩትንም ሊወነጅልና ሊያጋልጥ ይጥራል። አሳፋሪ ተልዕኮ። ሟቹን ጄኔራል ቁምላቸውን ኩዴታውን በማክሸፍ ይከሳል--ሰውየውን ጀግና ያሏቸው እስቲ ምላሽ ይስጡት።

ለዚያ ለታጋይ ትውልድ፣ ለኢሕአፓ አባላትና በትግሉ ለተሳተፉትና ስየል ለተቀበሉት ጀግኖች ሁሉ ያለኝ ጥሪ የሚከተለው ነው

- ይህን ታሪክን ማጅራት መቺ ሻምበልና መሰሎቹን ሁሉ ቸል ሳንል እንታገል! ለፖለቲካ እምባጮዎች መድረኩ አይለቀቅ
- በየቦታው ተደብቀው ያሉትን የቀይ ሽብር ወንጀለኞች ስም ዝርዝር እንሰብስብና ለወንጀላቸው የሚከፍሉበትን መንገድ እንፈልግ!!
- ለወያኔ ውድቀት በጋራ እንታገል!!